# ፍቅር እንደ መና

እምነት ሰላም ፍቅር ምስጋና ውዳሴ፣
በጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ፣
እንደ መና ሲወርድ ዓይተናል በዓይናችን፣
በእግዚአብሔር ሲመራ ቅዱስ እምነታችን።

ከአንድ እናት ተወልደው እንዳደጉ ልጆች፣
በፍቅር ይኖራሉ የሃይማኖት ሰዎች።
በፊት ጽድቁን እሹ ሌላው ይጨመራል፣
በማለት ክርስቶስ የተናገረው ቃል፣
እንዲህ እውን ሆኖ ለሁላችን ታየን፣
ሌላ ቃል የለንም እግዚአብሔር ይመስገን።

ለሃይማኖት ብንቆም ለሥርዓት ብንቀና፣
ከላይ ወረደልን ፍቅር እንደ መና።
ከሳሻችን ውደቅ ጠላታችን እፈር፣
በዓይናችን ዓይተናል ያጠርከው ሲሰበር።

የሥላሴ ልጆች ፍቅር ነው ስንቃችን፣
እምነተ ሙሉ ነን ለሃይማኖታችን።
በራችን ክፍት ነው ገርበብም አላለ፣
የአባቶቼን እምነት ሃይማኖቴን ላለ።
በጽርሐ አርያም በቅዱሱ ቦታ፣
አብረን እንቋደስ ከፍቅር ገበታ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አብርሃም ሰሎሞን
ነሐሴ ፳፮/፳፻፲ ዓ.ም.